# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# የአብክመ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ

# ተቋማዊ የአፈጻጸም መመሪያ

ነሀሴ 2014
<u>ባህር-ዳር</u>

## ማውጫ


1. መግቢያ ........ 4
2. አጭር ርዕስ ........ 4
3. የመመሪያው ዓላማ ........ 4
4. በየደረጃው ያሉ ፈጻሚ አካላት የስራ ድርሻ እና ሃላፊነት ........ 4
4.1. ክልል መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ........ 4
4.1.1. መስኖና ድሬኔጅ ጥናትና ዲዛይን ዳይሬክቶሬት ........ 4
4.1.2. መስኖና ድሬኔጅ ግምባታና ክትትል ዳይሬክቶሬት ........ 5
4.1.3. መስኖ ተቋማት አጠቃቀም፣ አስተዳደርና ጥገና ዳይሬክቶሬት ........ 6
4.1.4. መስኖ ተቋማት ግብዓት አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ........ 7
4.1.5. ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ........ 7
4.1.6. ዕቅድ፣ በጀት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ........ 8
4.1.7. ግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ........ 9
4.1.8. የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ........ 9
4.1.9. የሰው ሀብት ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ........ 10
4.1.10. ህግ አገልግሎት ........ 10
4.2. በዞን መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት መምሪያ ........ 11
4.2.1. መስኖና ድሬኔጅ ጥናትና ዲዛይን ቡድን ........ 11
4.2.2. መስኖና ድሬኔጅ ግምባታና ክትትል ቡድን ........ 12
4.2.3. መስኖ ተቋማት አጠቃቀም፣ አስተዳደርና ጥገና ቡድን ........ 13
4.2.4. ዕቅድ፣ በጀት ክትትልና ግምገማ ቡድን ........ 14
4.3. ወረዳ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ጽ/ቤት ........ 15
4.3.1. የመስኖ መሀንዲስ ቡድን ........ 15
4.3.2. ዕቅድ፣ በጀት ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ቡድን ........ 17
4.4. ስለሌሎች ተጠሪ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት ........ 17
4.4.1. ቆቦ ጊራና ሸለቆ ልማት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ........ 17
4.4.2. ሌሎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ........ 18
5. በየደረጃው ያሉ ፈጻሚ አካላት መከተል ስለሚኖርባቸው የአሠራር ስርዓት ........ 19
5.1. መስኖና ድሬኔጅ ጥናት እና ዲዛይን ........ 19
5.1.1. የመስኖ ጥናት እና ዲዛይን መነሻ ........ 19
5.1.2. አንድ የጥናት እና ዲዛይን ስራ ማለፍ ስለሚገባው መሰረታዊ ደረጃዎች ........ 20

5.2. መስኖና ድሬኔጅ ግንባታ ክትትል ........ 20
5.3. የመስኖ ተቋማት አጠቃቀም፣ አስተዳደርና ጥገና ........ 22
5.4. የመስኖ ተቋማት ግንባታ ግብዓት አቅርቦት ........ 23
6. የግንኙነት አግባብ ........ 24
6.1. ተቋማዊ ........ 24
6.2. ከባለድርሻ አካላት ጋር ስለሚኖር ግንኙነትና ትብብር ........ 25
7. ስለድጋፍና ክትትል ........ 25
8. የጌዜ ሰሌዳና መርሃ ግብር ........ 26

## 1. መግቢያ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የአስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር280/2014ዓ.ም መሠረት የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ በአዲስ መልኩ ሲቋቋም ለተቋሙ የተሠጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመፈጸም ያስችል ዘንድ ጎን ለጎን ተቋማዊ የአቅም ግንባታ ሥርዓት ይኖር ዘንድ የአጠቃላይ የፕሮጀክት ትግበራና አስተዳደር ወጥ በሆነ መልኩና በተቀመጠ አሠራር መፈፀም ይገበዋል፡፡ ስለሆነም ተቋሙ አዲስ እንደመሆኑ ከአሁን በፊት የራሱ አዋጅና መመሪያዎች ቢኖሩትም በአፈጻጸም የሚያጋጥሙ ችግሮች ማብራሪያ መስጠት ተገቢ በመሆኑ የራሱ የሆነ የፈጻጸም መምሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

ስለሆነም ተቋሙ ከክልል እስከ ወረዳ ያለው ፈፃሚና ባለድርሻ አካላት ሊከተሉት የሚገባ የአሠራር ስርዓት፣ የስራ ድረሻ እና የግንኙነት አግባብ በግልጽ ማስቀመጥ በማስፈለጉ ይህ ተቋማዊ የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአብክመ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ተቋማዊ አፈጻጸም መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

3.1 ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ ማስቻል፤

3.2 የፈጻሚ አካትን የመፈጸም አቅም ማሳደግና የባለድርሻ አካላትን ሚና ከፍ ማድረግ፤

3.3 ለቢሮ የተሰጡ ተግባርና ሃላፊነቶችን በብቃት ለማከናወን በፈጻሚ አካላት ወጥነት ያለው አሰራር እንዲኖር ማድረግ፤

3.4 በየደረጃው ያሉ ፈጻሚ አካላት የስራ ድርሻ በመለየት ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ማድረግ፤

3.5 ቢሮው በየደረጃው ካሉ ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ጋር በመርህ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲኖረው ማድረግ፤

## 4. በየደረጃው ያሉ ፈጻሚ አካላት የስራ ድርሻ እና ሃላፊነት

### 4.1. ክልል መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ

#### 4.1.1. መስኖና ድሬኔጅ ጥናትና ዲዛይን ዳይሬክቶሬት

- የክልሉን የውኃ ሀብት ለመስኖ አገልግሎት ለማዋል የጥናትና ዲዛይን ሥራዎችን ያከናውናል ወይም በሌሎች ያሠራል፣ቁጥጥር ያደርጋል፤
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በክልሉ ውስጥ በተለይም ቆላማና ከፊል ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች ያለውን የመስኖ ልማት አቅም ለመለየት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣

የውሀ እቀባና የአነስተኛ፣ የመካከለኛ እና ከፍተኛ መስኖ ፕሮጀክቶችን የጥናትና ዲዛይን ሥራዎችን ያከናውናል፣ እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ የአካባቢውን የግብርና መሬት ለማልማት የሚያስችል የመስኖ ልማት ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

- በፌደራሉ መንግሥት ባለቤትነት በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ክንውን ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፣ ውክልና ሲሰጠው የግንባታ ክትትል ሥራ ይሠራል፣ ያሠራል፤
- በመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ጥናት የመስኖ ውኃ ተጠቃሚው ተሳታፊና  እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- በክልሉ ውስጥ በጎርፍ አደጋ የሚጠቁ አካባቢዎች ቅድመ-ጥናት ያካሂዳል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎችን ይሠራል፡፡
- በክልሉ ውስጥ በግብረ ሠናይ ድርጅቶ የሚካሄዱ የመስኖና ድሬኔጅ ጥናትና ዲዛይን ስራዎች በመፈተሽ ወደ ስራ እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
- ከመስኖና ድሬኔጅ ጥናትና ዲዛይን ሥራዎች ጋር የተያያዙ ቴክኖሎጅዎች ጥራታቸውን የጠበቁና ስታንዳርዳቸውን ያሟሉ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በመፈተሽ ወደ ስራ እንዲገቡ ያበረታታል፣ ስልጠና ይሠጣል፤
- በዞኖችና በወረዳዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ይቆጣጠራል፤ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት አሠራሮችን ይዘረጋል፡፡

### 4.1.2. **መስኖና ድሬኔጅ ግምባታና ክትትል ዳይሬክቶሬት**

- የክልሉን የውኃ ሀብት ለመስኖ አገልግሎት ለማዋል የግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል ወይም በሌሎች ያሠራል፣ ግንባታቸው ጥራቱን ጠብቆ እንዲጠናቀቅ ያደርጋል፣ ግንባታው ሲጠናቀቅ ከገንቢው አካል ተረክቦ ለመስኖ ተቋማት አስተዳደር ያስረክባል፤
- በፌደራሉ መንግሥት ባለቤትነት በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ክንውን ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፣ ውክልና የግንባታ ሥራዎችን ይሠራል፣ ያሠራል፤
- በመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢው ኅብረተ-ሰብ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- የመስኖ ልማት ሽፋን እንዲያድግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- በመስኖ ልማት ሥራዎች ለሚሳተፉ አጋር አካላት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ የሚገነቡ የመስኖ አውታሮች ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በክልሉ ውስጥ በተለይም ቆላማና ከፊል ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች የውሀ እቀባና የአነስተኛ፣ የመካከለኛ እና ከፍተኛ መስኖ ግንባታዎችን

ያከናውናል፣ እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ የባህላዊ ወንዝ ጠለፋ ሥራዎች እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

- በክልሉ ውስጥ በጎርፍ አደጋ የሚጠቁ አካባቢዎች የመከላከያ ግንባታዎችን ይሠራል፣ ያስገነባል፤
- በክልሉ ውስጥ በግብረ ሠናይ ድርጅቶ የሚካሄዱ የመስኖና ድሬኔጅ የግንባታ ስራዎችን በመፈተሽ ወደ ስራ እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
- ከመስኖና ድሬኔጅ ግንባታ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ቴክኖሎጅዎች ጥራታቸውን የጠበቁና ስታንዳርዳቸውን ያሚሉ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በመፈተሽ ወደ ስራ እንዲገቡ ያበረታታል፣ ስልጠና ይሠጣል፤
- በዞኖችና በወረዳዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ይቆጣጠራል። ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት አሠራሮችን ይዘረጋል።

## 4.1.3. መስኖ ተቋማት አጠቃቀም፣ አስተዳደርና ጥገና ዳይሬክቶሬት

- ማህበራት ስለሚደራጁበት፣ አቅማቸው ስለሚገነባበትና ስለሚጠናከሩበት ሁኔታ በጥናት ላይ ተመሥርቶ ስልቶችን ያመነጫል፣ ልዩ ልዩ ስትራቴጅዎችን፣ መመሪያዎችን እንዲሁም የመገልገያ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤
- በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የመስኖ ተጠቃሚዎች ማኅበራትን ወይም ፌዴሬሽን አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችንና የማህበራት መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ-ደንቦችን መሠረት በማድረግ ያደራጃል፣ ይመዘግባል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
- ከማኅበራት መቋቋምና ተግባራቸውን ከማከናወን ጋር በተያያዘ ለዞንና ወረዳ አስፈጻሚ አካላትና ማህበራት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሠራል፤ የሙያ ድጋፍ ያደርጋል፤
- በክልሉ መንግሥት አማካኝነት የተገነቡ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የመስኖ ግድቦችን፣ ቦዮችንና ሌሎች የመስኖ አውታሮችን ተረክቦ ያስተዳድራል፣ ይንከባከባል፣
- በክልሉ ውስጥ የተገነቡ የመስኖ ተቋማት ዘላቂና ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የመለስተኛና ከፍተኛ ጥገና ሥራዎችን ያከናውናል ወይም በሌሎች ያሠራል፣ የጥገና ስራው ጥራቱን ጠብቆ እንዲጠናቀቅ ያደርጋል፣ሲጠናቀቅ ከገንቢው አካል ተረክቦ ለመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ያስረክባል፤
- የግንባታቸው የአገልግሎት ዘመናቸው አልቆ አገልግሎት የማይሠጡ የመስኖ ቋማትን የመልሶ ጥናትና ግንባታ ስራዎችን ይሠራል፤
- በፌደራሉ መንግሥት ባለቤትነት በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ክንውን ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፣ ተቋማትን ተረክቦ ያስተዳድራል፣
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በክልሉ ውስጥ በተለይም ቆላማና ከፊል ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች የተገነቡ የውሀ እቀባ፣ የአነስተኛ፣ የመካከለኛ እና ከፍተኛ የመስኖ የመስኖ አውታሮች የጥገና ሥራዎችን ያካሂዳል፣

- የመስኖ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ ከአስገንቢው አካል ጋር ርክክብ ይፈጽማል፤ የመጠቀም ጥያቄ ላቀረቡ ማህበራት ያስተላልፋል፡፡ ደህንነታቸውን ይቆጣጠራል ተገቢውን ጥገና በወቅቱ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
- በከፍተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ላይ ለአጠቃቀም እና አስተዳደር በሚያመች ሁኔታ እንዳስፈላጊነቱ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ይከፍታል፣ የተቀናጀ የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
- ከመስኖና ድሬኔጅ ተቋማት አስተዳደር ሥራዎች ጋር የተያያዙ ቴክኖሎጅዎች ጥራታቸውን የጠበቁና ስታንዳርዳቸውን ያሟሉ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፣ አዳዲስ አሠራሮችን ይዘረጋል፣ ቴክኖሎጅዎችን በመፈተሽ ወደ ስራ እንዲገቡ ያበረታታል፣ ስልጠና ይሠጣል፤
- ሁለትና ከዚያ በላይ ዞኖችን በሚያገለግል የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ላይ ማህበራት እንዲመሠረቱ፣ እንዲደራጁና ዓላማቸውን እንዲያሳኩ ተከታታይ ድጋፍ ያደርጋል፤
- የምዝገባ ጥያቄ ለሚያቀርብ ማህበር ለምዝገባ የሚያበቃዉን መስፈርት ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ በመስኖ ዉሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት መዝገብ ዉስጥ በመመዝገብ ለማህበሩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሠጣል፤
- የተቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን የሕግና የፋይናንስ ቁጥጥርና ምርመራ ያደርጋል፤
- ማህበራት በተቀመጠላቸው አሠራር መሠረት በአግባቡ መንቀሳቀሳቸውን እና ኃላፊነታቸውን በብቃት መወጣታቸውን ለማረጋገጥ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ምርመራ ያደርጋል፤ በውጤቱም መሠረት ለጠቅላላ ጉባኤ እያቀረበ ተገቢው እርምጃ መወሠዱን ያረጋግጣል፤
- በዞኖችና በወረዳዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ይቆጣጠራል፤ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት አሠራሮችን ይዘረጋል፡፡

### 4.1.4. መስኖ ተቋማት ግብዓት አቅርቦት ዳይሬክቶሬት

የክልሉን የግዥ መመሪያና የፕሮጀክቶችን የአሰራር መመሪያ መሰረት በማድረግ፡-

- የግንባታና የአማካሪ ግዥ ይፈጽማል፤
- ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት ያካሄዳል፤
- የውል ሰነድ ያዘጋጃል፤
- የጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል፤
- አጠቃላይ የግዥና አቅርቦት ሰነዶችን በአግባቡ ይይዛል፤
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

### 4.1.5. ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት

- አጠቃላይ የተቋም ተግባርና ሃላፊነት እንዲሁም አሰራርና አፈጻጸሞችን ለማህበረሰቡ በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች መረጃ ይሰጣል፤

- የትኛውም በመንግስት በጀት የሚመሩ የቢሮው መድረኮችና ስልጠናዎች ከቅድመ ዝግጅት ስራዎች ጀምሮ ለመድረኩ ስኬታማነት ሃላፊነት ወስዶ ያስተባብራል፣ እንደ አስፈላጊነቱ የአጋር አካላት መድረኮችን ድጋፍ ያደርጋል፤
- የተጠናቀቁ የመስኖ ግንባታ ርክክቦች እና የምርቃ ስነስርዓቶችን ያስተባብራል፤
- በመረጃ ነጻነት አዋጅ መሰረት ማንኛውም የተቋሙን አሰራር አስምልክቶ ለሚዲያ አካላት እና ለማህበረሰቡ ግልጽ መረጃ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- በየደረጃው መፈታት ያልቻሉ ፕሮጀክቶች ግንባታ ላይ የሚነሱ የማህበረሰብ ቅሬታዎችን እና አቤቱታዎች የሚፈቱበትን መንገድ ያመቻቻል፤
- ቢሮው በሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ የተሻለ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፉ የሚዲያና ኮሚኒኬሽን ስራ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይሠራል፤
- በመስኖና ድሬኔጅ ዙሪያ በማህበረሰቡና በተቋሙ ውስጥ ያሉ ዕውቀቶችንና ልምዶችን በማሰባሰብ ከአዳዲስ አሰራሮችና እውቀቶች ጋር የሚጣመሩበትንና የሚሸጋገሩበትን አግባብ ያስተባብራል፤
- ሌሎች ከመስኖና ድሬኔጅ ጋር የተገናኙ የህትመት ውጤቶችን ለማህበረሠቡ ያደርሳል፤
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

## 4.1.6. ዕቅድ፣ በጀት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት

- የተቋሙን የረዥምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ከሚመለከተው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ያስገመግማል፤
- የተቋሙን የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ያስገመግማል፣ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤
- የበጀት ምደባ፣ ግምገማና አፈጻጸም ይከታተላል፤
- የበጀት ዝውውርን መመሪያን መሠረት አድርጎ ያዘጋጃል፣ እንዲጸድቅም ክትትል ያደርጋል፤
- አጠቃላይ የፊዚካልና የፋይናንሻል አፈጻጸምን ከቢሮው ዕቅድ ጋር አያይዞ ክትትል ያደርጋል፣ ይገመግማል፣ ሪፖርት በመዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
- የመስኖ ልማት መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርዓትን ይዘረጋል፣ ያደራጃል፣ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል በየወቅቱ ያስተላልፋል፤
- የቢሮውን የኤሌክተሮኒክስና መገናኛ መሳሪያዎችን ደረጃ ያወጣል፣ ግዥ ሲፈጸም በደረጃቸው መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፣
- የቢሮው የኤሌክትሮኒክስና መገናኛ መሳሪያዎች ደህንነት እንዲጠበቁ የጥገናና የስርዓት ማሻሻል ስራዎችን ይሠራል፤
- ከህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ጋር በመሆን ለማህበረሠቡ የሚቀርቡ መረጃዎችን ያሳልጣል፤
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

## 4.1.7. ግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

- ስለክፍያ በክልልም ሆነ በዞን የመስኖና ድሬኔጅ ጥናትና ዲዛይን ወይም ግንባታ ስራ እንዲያከናውን ኃላፊነት ተሠጥቶች ውል የያዘው አካል በውሉ መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤ በውል አስተዳደሩ ሂደቱ የሚፈተሩ ችግሮችንም በኃላፊነት ይዞ መፍትሄ ይሠጣል፤
- በቢሮው የሚታዘዙ የመስኖና ድሬኔጅ የግንባታና የአማካሪ ክፍያ ሠነዳቸው መሟላቱን እያረጋገጠ በጊዜው ክፍያ ይፈጽማል፤
- በቢሮው የሚታዘዙ ሌሎች ክፍያዎችን መመሪያን መሠረት በማድረግ በጊዜው ክፍያ ይፈጽማል፤
- የሂሳብ የወጭና ገቢ የሂሳብ ሰነዶችን ከውስጥ ኦዲት፣ ከዕቅድ ዝግጅት እና ከባንክ ጋር ይናበባል፣ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየ15 ቀኑ ለቢሮ ኃላፊው ያቀርባል፤
- የቢሮውን ንብረትና ተሽከርካሪ በተቀመጠው የአሠራር መመሪያ መሠረት መዝግቦ ይይዛል፣ በየ3 ወሩ ያለውን ንብረት ለቢሮ ኃላፊው በሪፖርት ያሳውቃል፤
- ማንኛውንም ከንብረትና ፋይናስ የተገናኘ ሰነድ በአግባቡ ይሠንዳል፣ ሲጠየቅም ያቀርባል፤
- አጠቃላይ የፋይናንስና ግዥ አሠራር የክልሉን የገንዘብ ቢሮ የአሠራ መመሪያ፣ የፕሮጀክቶችንና የፕሮግራሞችን የሀብት አስተዳደር መመሪያ መሠረት አድርጎ ይፈጽማል፤
- ለቢሮው የሚያስፈልጉ የቁስ እና የአገልግሎት ግዥዎችን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ መመሪያን መሠረት አድርጎ ግዥ ይፈጽማል፤
- በተቋሙ ውስጥ አገልግሎት የማይሠጡ ቁሶችን ያስጠናል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የሚወገዱበትን አግባብ ያመቻቻል፤
- ከፋይናስና ንብረት አስተዳደር ጋር በተገናኝ አዳዲስ የአሰራር ስልቶችን ይነድፋል፣ እንዲተገበሩም ለቢሮ ያቀርባል፤
- ቢሮው የተቋቋመበትን ዓላማ ያሳካ ዘንድ የአሠራር ስርዓት በመዘርጋት የተሽከርካሪ ስምሪት ይሠጣል፤
- የተሽከርካሪ ስምሪት አሠራር እያዘጋጀ በቢሮው ያፀድቃል፤
- የነዳጅ አጠቃቀም ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲፈጸም አሠራር ይዘረጋል፤
- ተሽከርካሪዎች ወቅታዊ ጥገናና ፍተሻ እንዲያገኙ ያደርጋ፣ የክልሉን የመንገድ ትራንስፖርት መመሪያ በሚያዘው መሠረት ሌሎች ተግባሮችን እንዲፈጸሙ ያደርጋል፤
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

## 4.1.8. የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት

በየበጀት ዓመቱ፡-

- የፋይናንስ ኦዲት ያደርጋል፣
- የንብረት አስተዳደርና አያያዝ ኦዲት ያደርጋል፤

- የኦዲት ግኝትን መሠረት በማድረግ አዳዲስ አሠራሮችን ዘርግቶ ምርመራ ያደርጋል፣ በአሠራር እንዲመለሱ ያደርጋል፤
- የኦዲት ግኝቶችን መሠረት በማድረግ ከጠቅላይ ኦዲት ጋር በመሆን አጠቃላይ የተጠያቂነት አሠራር እንዲሠፍን ያደርጋል፤
- ቢሮው ውስጥ ከፍተኛ ሀብት በሚጠይቁ ተግባራትና ችግር ለፈጠሩ በሚችሉባቸው ክንዋኔ ላይ የተለየ የኦዲት ስርዓት በመስራት ሀብት እንዳይባክን ያደርጋል፣ ተጠያቂነትም እንዲሰፍን ይሠራል፤
- አጠቃላይ የውስጥ ኦዲት አሠራር የክልሉን የኦዲት አሰራር፣ የፕሮጀክቶችንና የፕሮግራሞችን የሀብት አስተዳደር መመሪያ መሠረት አድርጎ ይፈጽማል፤
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

## 4.1.9. የሰው ሀብት ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

- በሚቀርብ የቅጥር ጥያቄ መሰረት መመሪያን መሰረት አድርጎ የሰራተኛ ቅጥር ይፈጽማል
- የሰራተኛ ቅጥር የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እና የፕሮግራሞች የሰው ሀይል አሰተዳደር መመሪያ አሰራር በሚያዝዘው መሰረት ብቻ እንዲፈጸም ክትል ያደርጋል
- የሰራተኞችን ጥያቄ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እና የፕሮግራሞች የሰው ሀይል መመሪያ በሚያዝዘው መሰረት  በጽሁፍ ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል፤
- የሰራተኛውን የአቅም ግንባታ እና ስልጠና ያቅዳል ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን አፈጻጸሙን ይከታተላል የተሟላ መረጃ ይይዛል፤
- ልዩ ልዩ የመደብ፣ የትምህርት ዝግጅትና ጥቅማጥቅም ጥያቄዎችን በማሰባሰብና በመሰነድ ቢሮው ምላሽ እዲሰጥ ያደርጋል፤
- በመደብ፣ በደረጃ ዕድገት እንዲሁም ጥቅማጥቅምና ሌሎች የሚነሡ የሠራተኛ ጥያቄዎች በየደረጃው ለሲቪል ሠርቪስ ተቋማት ቀርቦ መታየትና ችግሮች ካልተፈቱ ተዋረዱን ጠብቆ ውሳኔ እየተሰጣቸው መምጣት ይኖርበታል፤
- አጠቃላይ የሰው ሃይል መመሪያን መሰረት አድርጎ ይሰራል፤
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

## 4.1.10. ህግ አገልግሎት

- ቢሮውን በሚመለከት በሚከሰቱ አለመግባባቶች ለፍትህ አካል ክስ እንዲመሠረት መረጃና ማስረጃ አጠናክሮ በጽሁፍ ያቀርባል፤

- በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ጉዳዩችን ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በወቅቱ ለቢሮው ኃላፊ ሪፖርት ያደርጋል፤
- በፍርድ ሂደት ላይ ላሉ ጉዳዩች ተጨማሪያ ማስረጃና የሰው ምስክር እንዲሟላ ከፍትህ አካል ጋር በቅርበት ይሠራል፤
- በፍርድ ውሳኔ አፈጻጸምና ብይን ላይ ቢሮው ቅሬታ ካለው ወቅታዊ የይግባኝ ጥያቄ እንዲቀርብ ከፍትህ አካሉ ጋር በቅርበት ይሠራል፤
- የፍትህና የክስ ማስረጃዎችና መረጃዎች ሚስጥራዊነትና ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ ያደራጃል፣ ይሰንዳል፣ በህግ አግባብ በተፈቀደለት አካል ብቻ ይሠጣል፤
- በፕሮጀክት አፈጻጸም  በሚነሱ አለመግባባቶች የፍርድ ሂደቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች አማራጮች ካሉ ለቢሮ በጽሁፍ ምክር ሀሳብ ያቀርባል፣ ለተፈጻሚነታቸው ክትትል ያደርጋል፤
- ቢሮው በሚይዛቸው የውል ሠነዶች ላይ የሚመለከተው የፍትህ አካል አስተያየት እንዲሰጥባቸው ያደርጋል፤
- ቢሮው በሚያዘጋጃቸው የአሰራር መመሪያዎች ላይ ከህግ አግባብ አስተያየት ይሠጣል፤

## 4.2. በዞን መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት መምሪያ

- የቢሮን ዕቅድና የወረዳዎችን ዕቅድ ታሳቢ ያደረገ ዞናዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ያስገመግማል፤
- የተገመገመ ወቅታዊ ሪፖርት ለቢሮውና ለሚመለከተው አካል ይልካል፤
- የህዝብ ግንኙነትን ስራ ከሚመለከተው የክልልና የዞን ተቋማት ጋር በመሆን በኃላፊነት ይዞ ይሰራል፤
- ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ከዋና ተግባር ጋር አስተሳስሮ ይሠራል፣ በሪፖርትም ያካትታል፤
- የዞን የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ያመቻቻል፤
- በዞኑ ውስጥ ለሚተገበሩ የመስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክቶች ላይ ለሚከሠቱ ችግሮች የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ያቅዳል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይፈታል፤

### 4.2.1. መስኖና ድሬኔጅ ጥናትና ዲዛይን ቡድን

- የዞኑን የውኃ ሀብት ለመስኖ አገልግሎት ለማዋል ከ100ሄ/ር በታች ለሚያለሙ ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ሥራዎችን ያከናውናል ወይም በሌሎች ያሠራል፣ቁጥጥር ያደርጋል፤

- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በዞኑ ውስጥ በተለይም ቆላማና ከፊል ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች ያለውን የመስኖ ልማት አቅም ለመለየት በሚደረገው ጥናትና ምርምር ድጋፍ ያደርጋል፤
- በዞኑ ውስጥ ለሚካሄዱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ክንውን ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፣ ውክልና ሲሰጠው የግንባታ ክትትል ሥራ ይሠራል፣ ያሠራል፤
- በመስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክቶች ጥናቶች ሲካሄዱ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚው ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- በዞኑ ውስጥ በጎርፍ አደጋ የሚጠቁ አካባቢዎች ቅድመ-ጥናት ያካሂዳል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎችን ይሠራል።
- በዞኑ ውስጥ በግብረ ሠናይ ድርጅቶች የሚካሄዱ የመስኖና ድሬኔጅ ጥናትና ዲዛይን ስራዎችን በመፈተሸ ወደ ስራ እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣
- በዞኑ ውስጥ ለሚገኙ ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍ ያደርጋል፤
- በወረዳዎች መካከል የሚካሄዱ የጥናትና ዲዛይን ስራዎችን የተሳለጡ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤
- በዞኑ ውስጥ የተጠኑና ለሚጠኑ የመስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክቶችን መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናክራል፤

## 4.2.2. መስኖና ድሬኔጅ ግምባታና ክትትል ቡድን

- የዞኑን የውኃ ሀብት ለመስኖ አገልግሎት ለማዋል ከ100ሄ/ር በታች የሆኑ የመስኖና ድሬኔጅ የግንባታ ሥራዎችን በኃላፊነት ይዞ ያከናውናል፣ ግንባታቸው ጥራቱን ጠብቆ እንዲጠናቀቅ ያደርጋል፣ ግንባታው ሲጠናቀቅ ከገንቢው አካል ተረክቦ የመስኖ ተቋማት አጠቃቀም፣አስተዳደርና ጥገና ቡድን ጋር በመሆን ለመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ያስረክባል፤
- በዞኑ ውስጥ ለሚካሄዱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ ክንውን ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤
- በመስኖና ድሬኔጅ ልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢው ኅብረተ-ሰብ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

- በመስኖ ልማት ሥራዎች ለሚሳተፉ አጋር አካላት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ የሚገነቡ የመስኖ አውታሮች ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በዞኑ ውስጥ በተለይም ቆላማና ከፊል ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች የውሀ እቀባና ከ100ሄ/ር በታች የመስኖና ድሬኔጅ ግንባታዎችን ያከናውናል፣ እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ የባህላዊ ወንዝ ጠለፋ ሥራዎች እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤
- በዞኑ ውስጥ በጎርፍ አደጋ የሚጠቁ አካባቢዎች የመከላከያ ግንባታዎችን ይሠራል፣ ያስገነባል፣
- በዞኑ ውስጥ በግብረ ሠናይ ድርጅቶ የሚካሄዱ የመስኖና ድሬኔጅ የግንባታ ስራዎችን በመፈተሽ ወደ ስራ እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣
- በዞኑ ውስጥ ለሚገኙ ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍ ያደርጋል፤
- በወረዳዎች መካከል የሚካሄዱ የግንባታ ስራዎችን የተሳለጡ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤
- በዞኑ ውስጥ የሚገነቡና የተገነቡ የመስኖና ድሬኔጅ ተቋማትን መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናክራል፤

### 4.2.3. **መስኖ ተቋማት አጠቃቀም፣ አስተዳደርና ጥገና ቡድን**

- በዞኑ ውስጥ የሚገኙትን የመስኖ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ያደራጃል፣ ይመዘግባል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
- በዞኑ ውስጥ የተገነቡ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የመስኖ ግድቦችን፣ ቦዮችንና ሌሎች የመስኖ አውታሮችን ከግንባታ ክትትል ቡድን ጋር በመሆን ለመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ያስረክባል፤
- በዞኑ ውስጥ የተገነቡ የመስኖ ተቋማት ዘላቂና ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የመለስተኛና ከፍተኛ ጥገና ሥራዎችን ያከናውናል ወይም በሌሎች ያሠራል፣ የጥገና ስራው ጥራቱን ጠብቆ እንዲጠናቀቅ ያደርጋል፣ሲጠናቀቅ ከገንቢው አካል ተረክቦ ለመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ያስረክባል፤
- የግንባታቸው አገልግሎት ዘመናቸው አልቆ አገልግሎት የማይሠጡ የመስኖ ቋማትን የመልሶ ጥናትና ግንባታ ስራዎችን ይሠራል፤

- በዞኑ ውስጥ የሚገነቡና የተገነቡ የመስኖ ተቋማትን ያስተዳድራል፣
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በዞኑ ውስጥ በተለይም ቆላማና ከፊል ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች የተገነቡ የውሀ እቀባ፣ የአነስተኛና የመካከለኛ የመስኖ የመስኖ አውታሮች የጥገና ሥራዎችን ያካሂዳል፣
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
- ከማኅበራት መቋቋምና ተግባራቸውን ከማከናወን ጋር በተያያዘ ለወረዳ አስፈጻሚ አካላትና ማህበራት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሠራል፤
- ሁለት ወረዳዎችን በሚያገለግል የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮች ላይ ማህበራትን እንዲመሠረቱ፣ አቅማቸው እንዲገነባ እና ዓላማቸውን እንዲያሳኩ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ በቢሮው ህጋዊ ሠውነት እንዲያገኙ ያደርጋል፤
- ማህበራት በተቀመጠላቸው አሠራር መሠረት በአግባቡ መንቀሳቀሳቸውን እና ኃላፊነታቸውን በብቃት መወጣታቸውን ለማረጋገጥ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ምርመራ ያደርጋል፤ በውጤቱም መሠረት ለጠቅላላ ጉባኤ እያቀረበ ተገቢው እርምጃ መወሠዱን ያረጋግጣል፤
- የመስኖ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ ከአስገንቢው አካል ጋር ርክክብ ይፈጽማል፤ የመጠቀም ጥያቄ ላቀረቡ ማህበራት ያስተላልፋል። ደህንነታቸውን ይቆጣጠራል ተገቢውን ጥገና በወቅቱ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
- በወረዳዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ይቆጣጠራል፤ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት አሠራሮችን ይዘረጋል።
- በወረዳዎች መካከል የሚካሄዱ የተቋማት አስተዳደር ፍትሀዊ የውኃ አጠቃቀምና ጥገና ስራዎችን የተሳለጡ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤
- የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ፌዴሬሽን ሲቋቋም በመረጃ አሰባበሰብና በተቋቋሙት ላይ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
- በዞኑ ውስጥ የሚገነቡና የተገነቡ የመስኖና ድሬኔጅ ተቋማትን መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናክራል፤

### 4.2.4. ዕቅድ፣ በጀት ክትትልና ግምገማ ቡድን

- የመምሪያውን የረዥምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ከሚመለከተው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ያስገመግማል፤

- የመምሪያውን የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ያስገመግማል፣ በመምሪያ ኃላፊው የተፈረመ ሪፖርት ለቢሮና ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤
- የበጀት ምደባ፣ ግምገማና አፈጻጸም ይከታተላል፤
- ከዞን ገንዘብ መምሪያ ጋር በመነጋገር ወቅታዊ የበጀት ዝውውር ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
- አጠቃላይ የፊዚካልና የፋይናንሻል አፈጻጸምን ከዞኑ ዕቅድ ጋር አያይዞ ክትትል ያደርጋል፣ ያስገመግማል፣ ሪፖርት በመዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
- ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

## 4.3. ወረዳ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ጽ/ቤት

- የወረዳውን የመልማት አቅምና የማህረሠቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ያስገመግማል፣ እንዲጸድቅም ለዞኑ ይልካል፤
- የተገመገመ ወቅታዊ ሪፖርት ለዞኑና ለሚመለከተው አካል ይልካል፤
- የህዝብ ግንኙነትን ስራ ከሚመለከተው የዞንና የወረዳ ተቋማት ጋር በመሆን በኃላፊነት ይዞ ይሰራል፤
- ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ከዋና ተግባር ጋር አስተሳስሮ ይሠራል፣ በሪፖርትም ያካትታል፤
- የወረዳ የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ያመቻቻል፤
- በወረዳው ውስጥ ለሚተገበሩ የመስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክቶች ላይ ለሚከሠቱ ችግሮች የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ያቅዳል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይፈታል፤

### 4.3.1. የመስኖ መሀንዲስ ቡድን

- የወረዳውን የውኃ ሀብት ለመስኖ አገልግሎት ለማዋል ከ50ሄ/ር በታች ለሚያለሙ ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ሥራዎችን ያከናውናል ወይም በሌሎች ያሠራል፣ቁጥጥር ያደርጋል፤
- በወረዳው ውስጥ ለሚካሄዱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን እና ግንባታ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፣ ውክልና ሲሰጠው የግንባታ ክትትል ሥራ ይሠራል፣ ያሠራል፤
- በመስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክቶች ጥናቶች፣ ግንባታዎችና ጥገናዎች ሲካሄዱ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚው ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- በወረዳው ውስጥ በጎርፍ አደጋ የሚጠቁ አካባቢዎች ቅድመ-ጥናት መረጃ ይሰበስባል፣ ለሚመለከተውም ወቅታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ይልካል፤

- በወረዳው ውስጥ በግብረ ሠናይ ድርጅቶችና አጋር አካላት የሚካሄዱ የመስኖና ድሬኔጅ ጥናትና ዲዛይን እና ግንባታ ስራዎችን በመፈተሽ ወደ ስራ እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣ይከታተላል፤
- በወረዳው ውስጥ ለሚገኙ ለቢሮው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍ ያደርጋል፤
- በወረዳው ውስጥ የተጠኑና ለሚጠኑ የመስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክቶችን መረጃ ይሰበስባል፣ ማህበር የተቋቋመባቸውንና ያልተቋቋመባቸውን ይለያል፣ ማህበር እንዲቋቋምባቸው ያደርጋል፤
- በወረዳው ውስጥ የሚገኙትን የመስኖ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ያደራጃል፣ በሚለከተው አካል እንዲመዘገቡ  ያደርጋል፤
- በወረዳው ውስጥ የተገነቡ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የመስኖ ግድቦችን፣ በዮችንና ሌሎች የመስኖ አውታሮችን ከአስገንቢው ጋር በመሆን ለመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ያስረክባል፤
- በወረዳው ውስጥ የተገነቡ የመስኖ ተቋማት ዘላቂና ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የአነስተኛ ጥገና ሥራዎችን በመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት በኩል እንዲሰራ ያደርጋል፣ በራሱም ይጠግናል፤
- በወረዳው ውስጥ የሚገነቡና የተገነቡ የመስኖ ተቋማትን ያስተዳድራል፤
- ከማኅበራት መቋቋምና ተግባራቸውን ከማከናወን ጋር በተያያዘ ለማህበራት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሠራል፤
- ሪፖርት ከመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበር የመቀበልና ግብረ መልስ ይሠጣል፤
- ማህበራት በተቀመጠላቸው አሠራር መሠረት በአግባቡ መንቀሳቀሳቸውን እና ኃላፊነታቸውን በብቃት መወጣታቸውን ለማረጋገጥ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ የኦድት ውጤቶችን መሠረት በማድረግ ለጠቅላላ ጉባኤ እያቀረበ ተገቢው እርምጃ መወሠዱን ያረጋግጣል፤
- በወረዳው የሚካሄዱ የተቋማት አስተዳደር ፍትሀዊ የመስኖ ውኃ አጠቃቀምና ጥገና ስራዎችን የተሳለጡ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤
- የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ፌዴሬሽን ሲቋቋም በመረጃ አሰባበሰብና በተቋቋሙት ላይ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
- በወረዳው ውስጥ የሚገነቡና የተገነቡ የመስኖና ድሬኔጅ ተቋማትን መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናክራል፤

- የመስኖ ስራው ከመጀመሩ በፊት የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በተጠቃሚዎች፣ በወረዳው.በዞንና በክልል የሚጠገኑትን የልየታ ስራ ይሠራል፤ ተጠቃሚውን በማስተባበር የካናልና የግድብ የደለል ጠረጋዎችን፣ መክፈቻ መዚጊያ በሮችን የማስተካከል ስራዎችን ያከናውናል፤ እንዲሁም ሌሎች ከውኃ አስተዳደርና ፍትሀዊ አጠቃቀም ጋር የተገናኙና በውክልና የሚሰጡ ስራዎችን ያከናውናል፡፡
- የውኃ መሳቢያ ሞተር ፓምፖችን ጥገና ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤

### 4.3.2. **ዕቅድ፣ በጀት ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ቡድን**

- የወረዳውን የረዥምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ከሚመለከተው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ያስገመግማል፤
- የወረዳውን የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ያስገመግማል፣ በጽ/ቤት ኃላፊው የተፈረመ ሪፖርት ለመምሪያውና ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤
- የበጀት ምደባ፣ ግምገማና አፈጻጸም ይከታተላል፤
- ከወረዳው ገንዘብ ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር ወቅታዊ የበጀት ዝውውር ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
- አጠቃላይ የፊዚካልና የፋይናንሻል አፈጻጸምን ከወረዳው ዕቅድ ጋር አያይዞ ክትትል ያደርጋል፣ ያስገመግማል፣ ሪፖርት በመዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
- ለወረዳው ተጠሪ ለሆኑ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

## 4.4. **ስለሌሎች ተጠሪ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት**

### 4.4.1. **ቆቦ ጊራና ሽለቆ ልማት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት**

- የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ያደራጃል፣ በሚመለከተው አካል እውቅና እንዲሠጠው ያሠጣል፤
- የተቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፤
- የተቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን የኦዲት ስራ ያከናውናል፤
- በኦዲት ግኝቱ መሠረት የማስተካካያ እርምጃ እንዲወሠድ ያደርጋል፤
- በኦዲት ግኝቱ ላይ ከማህበሩ ጋር ልዩነት ካለ ለዞን መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት መመሪያ እንዲታይ ይደረጋል፤

- በእያንዳንዱ የመስኖ ተቋም ከማህበሩ ጋር በመነጋገር መለስተኛ የጥገና ስራዎችን እንዲሠሩ ያደርጋል፤
- ከፍተኛ የመስኖ ጥገናዎችን ያከናውናል፤
- የግብዓትና ግብይት አቅርቦትና ስራ ከሚመለከተው አካል ጋር በትብብር ይሠራል፤
- የጥናትና ዲዛይን ስራዎች እንዲሠሩለት ቢሮውን በጽሁፍ ይጠይቃል፣ ሲፈቀድ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- ለመስኖ የጉድጓድ ቁፋሮ ስራ እንዲሰራለት ቢሮውን በጽሁፍ ይጠይቃል፣ ሲፈቀድ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- የጉድጓድ ጠረጋና ጥገና ስራዎችን በራሡ ያከናውናል፤
- የኃይል አቅርቦት ስራ ከሚመለከተው አካል ጋር በትብብር ይሰራል፤
- አዳዲስ የመስኖ ተቋማት እንዲገነቡለት ቢሮውን በጽሁፍ ይጠይቃል፣ ሲፈቀድ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- የሰው ኃይል አስተዳደርና ተያያዥ ስራዎችን መመሪያን ተከትሎ በራሱ ይሠራል፤
- ከተቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን በማስተባበር የጥገናና ስራ ማስኬጃ ወጪዎች እንዲያዋጡ በማድረግ የመለዋወጫ እቃዎችን እንዲቀርቡ ያደርጋል፣ አሠራርን በሚመለከተው አቅርቦ ያጸድቃል፤
- ዓመታዊ፣ የመንፈቅና የሶስት ወር ሪፖርት ጊዜውን ጠብቆ ለቢሮው ያቀርባል፤
- በአገልግሎት ክልሉ ውስጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የውኃ ክብካቤና አስተዳደር ስራዎችን ይሠራል፤
- አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን ያላምዳል፣ ይተግባራል፤
- አነስተኛ ወርክ ሾብ በማቋቋም በራሱ የሞተር፣ ፓምፕና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ይጠግናል፤

## 4.4.2. **ሌሎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት**

- የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ያደራጃል፣ በሚመለከተው አካል እውቅና እንዲሠጠው ያሠጣል፤
- የተቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፤
- የተቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን የኦዲት ስራ ያከናውናል፤

- በኦዲት ግኝቱ መሠረት የማስተካካያ እርምጃ እንዲወሠድ ያደርጋል፤
- በኦዲት ግኝቱ ላይ ከማህበሩ ጋር ልዩነት ካለ ለዞን መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት መመሪያ እንዲታይ ይደረጋል፤
- በእያንዳንዱ የመስኖ ተቋም ከማህበሩ ጋር በመነጋገር መለስተኛ የጥገና ስራዎችን እንዲሠሩ ያደርጋል፤
- ከፍተኛ የመስኖ ጥገናዎችን ያከናውናል፤
- የግብዓትና ግብይት አቅርቦትና ስራ ከሚመለከተው አካል ጋር በትብብር ይሠራል፤
- የኃይል አቅርቦት ስራ ከሚመለከተው አካል ጋር በትብብር ይሰራል፤
- አዳዲስ የመስኖ ተቋማት እንዲገነቡለት ቢሮውን በጽሁፍ ይጠይቃል፣ ሲፈቀድ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- የሰው ኃይል አስተዳደርና ተያያዥ ስራዎችን መመሪያን ተከትሎ በራሱ ይሠራል፤
- ከተቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን በማስተባበር የጥገናና ስራ ማስኬጃ ወጪዎች እንዲያዋጡ በማድረግ የመለዋወጫ እቃዎችን እንዲቀርቡ ያደርጋል፣ አሠራርን በሚመለከተው አቅርቦ ያጸድቃል፤
- ዓመታዊ፣ የመንፈቅና የሶስት ወር ሪፖርት ጊዜውን ጠብቆ ለቢሮው ያቀርባል፤
- በአገልግሎት ክልሉ ውስጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የውኃ ክብካቤና አስተዳደር ስራዎችን ይሠራል፤
- አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን ያላምዳል፣ ይተግባራል፤

# 5. በየደረጃው ያሉ ፈጻሚ አካላት መከተል ስለሚኖርባቸው የአሠራር ስርዓት

## 5.1. መስኖና ድሬኔጅ ጥናት እና ዲዛይን

ቴክኒካዊ የሙያ ስብጥር እና አካሔድ የመስኖ ተቋማት የጥናት እና ዲዛይን አዳጊና አለም አቀፋዊ ባህር ስላለው አሁን በተደረሰበት ደረጃ የጥናት መነሻው የፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ከክልሎች ጋር በመሆን ያስጠናው ባለ 30 ጥራዝ ሰነድ እንደ ስራ መመሪያ ይወሰዳል፡፡

### 5.1.1. የመስኖ ጥናት እና ዲዛይን መነሻ

ሀ. ከመስኖ ተጠቃማዎች /አርሶ አደሮች/ የይጠናልን ጥያቄ በወረዳ እና ዞን መዋቅር በኩል መነሻ ሊሆን ይችላል፤

ለ. የቢሮው ባለሙያዎች ወይንም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ስለአዲሱ ፕሮጀክት ዝርዝር መነሻ በሚያቀርቡት ላይ መነሻ ሊሆን ይችላል፤

ሐ. በተለየ መልኩ ከክልሉ መንግስት የሚሰጥ አቅጣጫ ካለ እንደ መነሻ ሊወሰድ ይችላል፤

5.1.2. **አንድ የጥናት እና ዲዛይን ስራ ማለፍ ስለሚገባው መሰረታዊ ደረጃዎች**

ሀ. የልየታ ስራ (Site-identification)

ለ. የቅኝት ጥናት (Reconnaissance & prefeasibility)

- ውጥን የጥናት ሪፖርት የተሠነደ (Inception Report)
- ውጥን የጥናት ሪፖርት ግምገማ (Inception Report Review)
- መረጣ (Screening)

ሐ. ዝርዝር ያዋጭነት ጥናት (Detail Feasibility study)

- የባለድርሻ አካላት ውይይት እና ግምገማ (Stake holder Review)

መ. የመጨረሻ ጥናትና ዲዛይን / final Study and design/

ሠ. መሬት ላይ የማረጋገጥ ስራ /Ground truth /

- በጸደቀ የጥናትና ዲዛይን የመሬት ላይ ማረጋገጫና መረካከቢያ ቅጽ መሠረት፤

ረ. ያለቀለት የጥናት ሠነድ ርክክብ (Document handover)

- የመጨረሻ የጥናትና ዲዛይን ሠነድ መረካከቢያ ቅጽ (Format)፤
- የወረቀት ህትመትና ኤሌክትሮኒክ ሰነድ (Hard copy & soft copy as agreement)

## 5.2. መስኖና ድሬኔጅ ግንባታ ክትትል

5.2.1 ተሟላ ጥናትና ዲዛይን እና በወቅቱ የተገመገመ ሰነድ መኖሩን ማረጋገጥ፤

5.2.2 ወደ ግንባታ ከመገባቱ በፊት የይገንባልን ጥያቄ ከአርሶ አደሮች መነሻ ሆኖ በወረዳ እና በዞን መዋቅር ጥያቄ በጽሁፍ መቅረብ ይኖርበታል፤

5.2.3 ግንባታው ከመጀመሩ በፊት የባላድርሻ አካላት ተግባር እና ሀላፊነት በግልጽ ቀርቦና ውይይት ተደርጎበት የስምምነት ፊርማ በባለድረሻ አካላት መግባቢያ ሠነድ ቅጽ መሠረት መካካሄድ አለበት እንዲሁም በህዝብ ግንኙነት የታጀበ የማስጀመሪያ መድረክ መካሄድ አለበት፤

5.2.4 ከግንባታ በፊት ሁለት ሰነዶች መፈረም ይገባቸዋል፤

ሀ. ሙያዊ የግንባታ ቦታ ርክክብ ሰነድ /ውልን እና የጥናት እና እና ዲዛይን ሰነድ መነሻ ያደርጋሉ/

ለ. የባለድርሻ አካላት መግባቢያ ሰነድ፤

5.2.5 በአዋጁ፣ በደንቡና መመሪያው መሠረት የተደራጁ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበር መኖርና ሙሉ ሂደቱን መከታተልና በሳይት ርክክቡ ሠነድ ላይ መፈራረም አለባቸው፤

5.2.6 የግንባታ ክትትልና ድጋፍ፡-

ሀ. በተቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት በኩል ክትትልና ድጋፍ መደረግ ይኖርበታል፤

ለ. ከ50 እስከ 100ሄክታር የሚገነቡ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮች በወረዳው አብይ ኮሚቴ ክትትልና ድጋፍ መደረግ ይኖርበታል፤

መ. ከ100ሄክታር በላይ ለሆኑ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮች በዞኑ አብይ ኮሚቴ ክትትልና ድጋፍ መደረግ ይኖርበታል፤

ሠ. የክትትል መሀንዲስ-ተጠሪነቱ ለመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበር፣ ለወረዳው አብይ ኮሚቴ፣ ለዞን አብይ ኮሚቴ እና ውል አስተዳደርን በተመለከተ ተጨማሪ ተጠሪነቱ ውል ለሰጠው አካል ይሆናል፤

ረ. በግንባታ ሂደት አዲስ የስራ ዓይነት ሲከሰት የክትትል መሃንዲሱ የስራውን አስፈላጊነት ቴክኒካዊ ማብራሪያ ያቀርባል፤ ይህ ማብራሪያ በዞኑ ወይም በቢሮው ተቀባይነት ካገኘ ተቋራጩ የመስሪያ ዋጋ እንዲያቀርብ ይደራጋል፤

ሰ. የክትትል መሃንዲሱ የራሱን አዲስ ነጠላ ዋጋ ሰርቶ ለቢሮው በፕሮጀክት አማካሪ ድርጅቱ በኩል ለቢሮው ይቀርባል፣ የሚመለከተው ዳሬክተር/ቡድን/ አዲስ የነጠላ ዋጋ የሚሰራ ቡድን አቋቁሞ ለውሳኔ በሚያመች መልኩ በቃለ ጉባኤ የተደገፈ እና የተገመገመ ሰነድ ለማኔጅመንቱ በማቅረብ ማኔጅመንቱ የቀረበውን የነጠላ ዋጋ ጥያቄ በ7 ቀን ውስጥ ባልበለጠ ውሳኔ ማሳረፍ አለበት፤ ይህ አሰራር በዞን እና በወረዳ በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ሸ. አዲስ የነጠላ ዋጋ ይጽደቅልን ጥያቄ የተለየ ነገር እስከሌለ ድረስ ግንባታው ከመፈጸሙ በፊት ቀርቦ ውሳኔ የተሠጠበት ሊሆን ይገባል፤

5.2.7 ግንባታው ስለተጠናቀቀ ተቋም ርክክብ

ሀ. በተወሠደው የግንባታ ውል እና በመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበር ማቋቋሚያና ማስተዳደሪያ መመሪያ ቁጥር 02/2013ዓ.ም አንቀጽ 46 መሰረት አንድ የመስኖ ተቋም ከተጠናቀቀ እና ወደ ልማት መግባት እንደሚችል ከተረጋገጠ በኋላ ለዚሁ

ተግባር ተብሎ በቢሮው በተዘጋጀው የመጀመሪያና የመጨረሻ ርክክብ ሰነዶች መሠረት አስገንቢው ከገንቢው አካል ጋር ርክክብ መፈጸም ይኖርበታል፤

ለ. አስገንቢው አካል የተረከበውን የመስኖና ድሬኔጅ ተቋም የመስኖ አጠቃቀም፣ አስተዳደርና ጥገና ዳይሬክቶሬት/ቡድን/ ባለበት ተቋሙን እንዲጠቀሙበት፣ እንዲያስተዳድሩትና እንዲንከባከቡት ለመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበር ርክክብ መፈጸም ይኖርበታል፤

5.3. **የመስኖ ተቋማት አጠቃቀም፣ አስተዳደርና ጥገና**

5.3.1 የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ለማቋቋም መከተል ስለሚገባ የአሠራር ስርዓት፡-

ሀ. የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት አዋጁን፣ ደንቡንና ማስፈጸሚያ መመሪያውን በየደረጃው ላሉ አካላት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ መስራት፤

ለ. በቢሮ፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ ማህበር ስለሚቋቋምበት የመስኖ ተቋም መረጃዎችን መሠብሠብ፤

ሐ. የመስክ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ(አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ተቋማዊ ሁኔታዎች እና ሌሎችን መረጃዎች ማየትና ውይይት ማካሄድ)፤

መ. ለተጠቃሚው የግንዛቤ ፈጠራ ስራ በመስራት ለሚመሠረተው ማህበር መስራች ኮሚቴ ማስመረጥ፣ የመመዝገቢያ ክፍያ ማስወሠን፤

ሠ. ለመስራች ኮሚቴው ስልጠና መስጠት፤

ረ. የመመስረቻ ሠነዶችን ማርቀቅ፣ የመመዝገቢያ ክፍያ መሠብሠብ፤

ሰ. 50+1 ተጠቃሚ ለሆኑ ከሚችሉት ውስጥ የመመዝገቢያ ክፍያ መክፈላቸውና የማህበሩ አባል መሆናቸው ሲረጋገጥ የምስረታ ጉባዔ ማካሄድ (የመመስረቻ ሠነዶችን ማጸደቅ፣ አመራር አካላትን ማስመረጥ) ፤

ሸ. የምስረታ ሰነዶችን በማሟላት የስራ አመራር ኮሚቴው መተዳደሪያ ደንብ፣ ውስጠ-ደንብና የምስረታ ቃለ-ጉባኤው ገጽ በገጽ እንዲፈርምበት በማድረግ ማህበሩን ማስመዝገብ፤

5.3.2 ከዚህ በፊት የተቋቋሙ ማህበራትን የክትትልና ድጋፍ ስራ መስራት፤

5.3.3 የተቋቋሙ ማህበራትን የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ስራ መስራት፤

5.3.4 በማህበራት መካከል የሚፈጠሩ የመስኖ ውኃ ግጭቶችን ለመፍታት፣ ከላይ እስከ ታች የመስኖ ውኃ መገኛና ማስተላለፊያውን ለመንከባከብ፣ የውኃ ሀብቱን በአግባቡ

ለማስተዳደርና ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን ደንቡና መመሪያውን መሠረት አድርጎ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ፌዴሬሽንን ያቋቁማል፤

5.3.5 የመስኖ አውታር ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ተቋማት በመለየት ጥናትና ዲዛይን በተቀመጠው ሙያዊ የአሠራ ሥርዓት መሠረት በማድረግ መስራት፤

5.3.6 የመስኖ አውታር ጥገና ወይም መልሶ ማቋቋም ግንባታ በተቀመጠው ሙያዊ የአሠራ ሥርዓት መሠረት ማካሄድ፤

5.3.7 የተጠናቀቁ ግንባታዎች ከአስገንቢው አካል ጋር በመሆን ለመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ያስተላልፋል፤

## 5.4. የመስኖ ተቋማት ግንባታ ግብዓት አቅርቦት

5.4.1. እንደየ በጀት ምንጫቸው ለዘመኑ የተከለሰ የግዥ መመሪያ ሰነድ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፤

5.4.2 የመስኖና ድሬኔጅ ስራዎች ወቅታዊ የዋጋ ጥናት በየ3ወሩ ያካሂዳል፤

5.4.3. የመስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክት የአማካሪ ግዥ ይፈጽማል፤

5.4.4. የመስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክት የግንባታ ግዥ ይፈጽማል፤

5.4.5. አጠቃላይ የግዥ ስርዓት የክልሉን የገንዘብ ቢሮ የአሠራ መመሪያ፣ የፕሮጀክቶችንና የፕሮግራሞችን የግዥ መመሪያ መሠረት አድርጎ ይፈጽማል፤

5.4.6. የጨረታ ሂደት ቀደም ተብሎ በተረጋገጠ እና በጸደቀ የግዥ መመሪያ ይፈጽማል፤

5.4.7. የጨረታ ሠነዶችን በግዥ መመሪያው መሠረት ይሠንዳል፤

5.4.8. ማንኛውም የመስኖና ድሬኔጅ ግዥ ሲፈጸም የጨረታ ሂደቱን የሚያስፈጽሙ ባለሙያዎችና አጽዳቂ ኮሚቴዎችን በዳይሬክቶሬቱ አቅራቢነት በቢሮው ሀላፊ ብቻ ይሾማሉ፤

5.4.9. የጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን ሰነድ ከመጽደቁ በፊት በቢሮው በተሾሙ አጽዳቂ ኮሚቴ መታየት እና አስተያየት መቅረብ ይገባዋል፤

5.4.10. የአጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢ በምክትል ቢሮ ኃላፊ የሚመራ ሆኖ ሌሎች ሁለት ባለሙያዎች በቢሮ ኃላፊ በደብዳቤ ይወከላሉ፤

5.4.11. በአጽዳቂ ኮሚቴ የታየ ሰነድ 2 ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንዲጸድቅ ለቢሮ ኃላፊው ወይም ለተወካይ መቅረብ አለበት፤

5.4.12. የተለየ ነገር እስከሌለ ድረስ ኃላፊው በ5 ቀን ውስጥ ሊያፀድቀው ወይም ግዥውን ሊሰርዝ ይችላል፤

5.4.13. የፀደቀ የጨረታ ሰነድ ውጤት በግልፅ በሰሌዳ ላይ መለጠፍ አለበት፤ በጨረታው ላልተሳካላቸው ተጫራቾች ያላሟሉት ነጥቦች ከነምክንያታቸው በደብዳቤ ሊገለጽላቸው ይገባል፤

5.4.14. ያልተሳካላቸው ተጫራቾች ቅሬታ ካላቸው በ5 ቀን ውስጥ ቅሬታቸውን በፁሁፍ ብቻ ማቅረብ ይገባቸዋል /በማስታወቂያ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ የሚያዝ የስራ ቀናት ይሆናል/፤

5.4.15. ጫራታውን ያሸነፈ ተቋራጭ መቀበሉን በደብዳቤ ማሳወቅ ይገባዋል፤

# 6. ሃላፊነትና ተጠያቂነት

6.1- ቢሮው ውል ወስዶ በሚያስገነባቸው እና በሚያስተዳድራቸው ማንኛውም ግንባታዎች ላይ ለሚከሰቱ እና ለሚነሱ የፍርድቤት ክሶች እና ተያያዥ ጉዳዮች ሙሉ ሃላፊነት ይወስዳል፤

6.2- የዞን መምሪያ በራሱ ውል ወስዶ ለሚያስገነባቸው እና ለሚያስተዳድራቸው የመስኖ ተቋማት ላይ የሚነሱ ክስ ራሱን ችሎ ይከራከራል በብይን አፈጻጸምም ሙሉ ሃፊነት ራሱ ይወስዳል፤

6.3- ወረዳ ራሱ ውል ወስዶ ለሚያስገነባቸው እና ለሚያስተዳድራቸው ማንኛውም ግንባታ የሚነሱ ክስ ራሱን ችሎ ይከራከራል በብይን አፈጻጸምም ሙሉ ሃፊነት ራሱ ይወስዳል፤

# 7. የግንኙነት አግባብ

## 7.1. ተቋማዊ

6.1.1 በጸደቀው እቅድ መሠረት ቢሮው ወደ ዞን ስራ ክፍሎ ይሠጣል፤ በተመሳሳይ ዞን ለወረዳ ይሠጣል፤

6.1.2 የሪፖርት ቅብብሎሽን በተመለከተ ከባለሙያ የመጣ ሪፖርት በቡድን ይገመገምና በቡድን መሪው በኩል ለመምሪያ/ጽ/ቤት ሪፖርት ይደረጋል፣ የመምሪያ ኃላፊው/ጽ/ቤት ኃላፊው የቀረበውን ሪፖርት በማኔጅመንት አስገምግሞ ለሚመለከተው አካል ይልካል፤

6.1.3 የሪፖርትን አስምልክቶ የሩብ ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ከ15-20 ባለው ቀናት ውስጥ ከዞን እና ከወረዳ የተጠቃለለ ሪፖርት ለቢሮው ይቀርባል።

6.1.4 ቢሮው የቀረበውን ሪፖርት አይቶ ሩብ ዓመቱ ባለቀ የመጀመሪያው 5 ቀናት ውስጥ ግብረመልስ ለመምሪያዎች ይሰጣል፤በተዋረድ መምሪያዎች በ5 ቀን ውስጥ ለወረዳዎች ግብረመልስ ይሰጣሉ፤

6.1.5 ቢሮው በማኔጅመንት የተገመገመ እና ከዞን መምሪያ ጋር የጋራ የተደረገ የተጠቃለለ ክልላዊ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ሩብ ዓመቱ ባለፈ በ10 ቀናት ውስጥ ያቀርባል፤

6.1.6 ሞያዊ ሪፖርቶችን በተመለከተ የዞን የስራ ቡድኖች ለክልል ዳሬክተሮች በየ15 ቀኑ በኢሜል ወይም በቴሌግራም ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ መለዋወጥ ይገባቸዋል፤ በተመሳሳይ የወረዳ ቡድን ከዞን ቡድኖች ጋር የሪፖርት ቅብብሎሽ ያደረጋሉ፡፤

6.1.7 የተቋሙ ኮር አመራር፣ ማኔጅመንት፣ ዳሬክተሮችና ሞያተኞች፣ ቡድነ መሪዎችና ሞያተኞች እንዲሁም አጠቅላላ ሰራተኞች ጋር የሚካሄዱ መድረኮችም ሆኑ የስራ ግንኙነት አግባባቦች የክልሉን የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባስቀመጠው መመሪያ መሰረት ይሆናል። ሁሉም የስራ በግንኙነቶች ስራን በሚያሳልጥ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በሰነድ የተደገፉ ይሆናሉ፤፤

## 7.2. ከባለድርሻ አካላት ጋር ስለሚኖር ግንኙነትና ትብብር

6.2.1 በየሩብ ዓመቱ ቢሮው የሶስትዮሽ ውይይት መድረክ ያካሄዳሉ፤ውይይቱም በቃለ ጉባኤ ተደግፎ ለቀጣይ ውይይት እንደመነሻ ይወሰዳል፤

6.2.2 በየሩብ ዓመቱ የዞን መምሪያዎች የሶስትዮሽ ውይይት መድረክ ያካሄዳሉ፤ውይይቱም በቃለ ጉባኤ ተደግፎ ለቀጣይ ውይይት እንደመነሻ ይወሰዳል፤

6.2.3 እደንደየ አስፈላጊነቱ በፐሮጀክት አፈጻጸም ላይ እንከን ሲገጥም ተናጥላዊ የሆነ የሶስትዮሽ ውይይት መነሻ ጥያቄ መሰረት ተደርጎ በ5 ቀን ውስጥ ሊካሄድ ይገባል፤ ይህ የሶስትዮሽ ውይይት ችግሩ በተፈጠረበት ወረዳ ወይም ዞን የሚካሄድ ሆኖ መድረኩ የአካባቢውን አመራር እና የመስኖ ኮሚቴዎችን ያካተተ ይሆናል፤

6.2.4 ቢሮው በተለየ መልኩ ፕሮጀክት ተኮር የሆኑ የዞን እና የወረዳ አስተዳደር፣ መሬት፣ ግብርና፣ ፍትህ አካል፣ ስራና ስልጠና እንዲሁም አካባቢ ጥበቃ ተቋማት ጋር በየ6 ወሩ የጋራ ውይይት ይኖራል፤

6.2.5 ከሚንስቴር መ/ቤቱ መደበኛ የዕቅድ ዝግጅት ግምገማ እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በሚፈጠሩ መድረኮች ወይም ቢሮው በሚያዘጋጃቸው መድረኮች ችግር ፈች በሆነ መልኩ ተሳትፎ ያደርጋል፤

6.2.6 ሌሎች አበዳሪና አጋር አካላት ጋር ወቅታዊ የሆነ መድረኮች ይዘጋጃሉ ወይም በተዘጋጁት መድረኮች ላይ ቢሮው ተሳትፎ ያደርጋል፤

# 8. የማበረታቻና ሽልማት ስርዓት

8.1- በተቀመጠው የሲቪል ሰርቪስ መመሪያ አሰራር መሰረት ስራን በትብብርና በውድድር መንፈስ ለመፈጸም ያስችል ዘንድ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት የግድ ይላል።

ስለሆነም በየዓመቱ ቢሮው ከአንድ እስከ ሶስት የወጡ መምሪያዎችን እንዲሁም ዞኖች በስራቸው ያሉ ወረዳዎችን አወዳድረው በሚያመጡት መሰረት አንድ ወረዳ በየዓመቱ የማበረታቻ ሽልማት ያገኛል። ይህ የማበረታቻ ሽልማት ተቋማት የተቀላጠፈ አሰራር እና የመልካም አስተዳዳር ችግሮቻቸውን ለመፍታት የሚያግዝ ሆኖ እንደ አቅሞቻቸው ተፈጻሚ

ያደርጋሉ። የማወዳደርያ መስፈርቶች ቢሮው በዝርዝር አይቶ ያጸደቀውን ቀድሞ ሁሉም ዞኖች እንዲያውቁት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል፤

## 9. ስለድጋፍና ክትትል

7.1 በዓመት ሁለት ጊዜ የቢሮው የማኔጅመንት የመስክ ድጋፍና ክትትል ያደረጋል ጊዜውም ታህሳስ እና ግንቦት ወራት ውስጥ ይሆናል፤

7.2 ቢሮው በዓመት ሁለት ጊዜ የ6 ወር ዕቅድ አፈጻጸም እና የመስክ ድጋፍና ክትትል ሪፖርት የዞን እና የወረዳ ማኔጅመንት በተገኙበት መድረክ ይዘጋጃል፤

7.3 በየሩብ ዓመቱ ቢሮው መድረክ በማዘጋጀት የዞን መምሪያዎችን አፈጻጸም ይገመግማል፤

7.4 በተመሳሳይ በዓመት ሁለት ጊዜ የዞን ማኔጅመንት የመስክ ድጋፍና ክትትል በወረዳ ይደረጋል ጊዜውም ህዳር እና ሚያዚያ ወራት ውስጥ ይሆናል፤

7.5 ሁሉም ዞኖች በዓመት ሁለት ጊዜ የ6 ወር ዕቅድ አፈጻጸም እና የመስክ ድጋፍና ክትትል ሪፖርት የወረዳ ማኔጅመንት በተገኙበት መድረክ ይዘጋጃል፤

7.6 በየሩብ ዓመቱ መምሪያዎች መድረክ በማዘጋጀት የወረዳን ጽ/ቤቶች አፈጻጸም ይገመግማሉ፤

7.7 የመስክ ድጋፍና ክትትል በቢሮው ማኔጅመንት የጸደቀ የድርጊት መርሃ ግብር/ ToR/ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

7.8 እንደ አስፈላጊነቱ በስልክ፣ በኢሜል፣ በቴሌግራም እና በሌሎች መገናኛ አማራጮች በመጠቀም ስራን ማሳለጥ ይጠበቃል፤

7.9 የፕሮጀክቱ አፈጻጸም በመስክ ላይ በመገኘት የድጋፍና ክትትል ስራ ይሰራል፣ /ተቋራጭ፣አማካሪ፣የመስኖ ተጠቃሚዎች እና ሌሎች አካላት/ በተገኙበት ይካሄዳል፣ ውልን መሰረት አድረጎ የተላለፉ ውሳኔዎች መፈጻማቸውን ይከታተላል፣ ቢያንስ አንድ ፕሮጀክት በዓመት ሁለት ጊዜ በኮር አመራሩ ክትትልና ድጋፍ ስራ መሰራት ይገባል፤

7.10 የታቀዱ ስራዎችን በዕውቀት ላይ ተመስርቶ ለማከናወን በየደረጃው የሙያ ስልጠናዎች ይሠጣሉ፤

## 10. የጊዜ ሰሌዳና መርሃ ግብር

8.1 ከሃምሌ 1 እስከ መስከረም 30 የዝግጅት ምዕራፍ ይሆናል፤

8.2 ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 30 የተግባር ምዕራፍ ይሆናል፤

8.3 ከግንቦት 1 እስከ ሰኔ 30 የማጠቃለያ ምዕራፍ ይሆናል፤

## 11. የተቋሙ ማስፈጸሚያ ህጎች

11.1 የአስፈጻሚ አካላት ተግባርና አሃላፊነት ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 280/2014

11.2 የኢፊድሪ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ማደራጃ 841/2006

11.3 የአብክመ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራትማቋቋሚያና ማስተዳደሪያ 239/2008

11.4 የአብክመ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ማቋቋሚያና ማስተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 190/2012

11.5 የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ማቋቋሚያና ማስተዳደሪያ መመሪያ ቁጥር 02/2013

11.6 የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት የሂሳብ አያያዝ ረቂቅ መመሪያ

11.7 የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት የኦዲት ረቂቅ መመሪያ

11.8 በየዓመቱ የጸደቀ የፌደራል እና የክልሉ የግዥ መመሪያ

11.9 የፌደራል እና የክልሉ የፋይናስ አስተዳደር መመሪያ

11.10 የፌደራል እና የክልሉ የኦዲት መመሪያ

11.11 የሲቪል ሰርቪስ የተለያዩ መመሪያዎች

11.12 የክልሉ የተሸሻለው የአካባቢና የማህበረሰብ ደህንነት አጠባበቅ መመሪያ

11.13 የመሬት አስተዳደር፣አጠቃቀም መመሪያ

11.4 የፌደራል የውሃ ሃብት አስተዳዳር  አዋጅና ደንብ

## 12. አባሪ ቅጻቅጾች